# *Tawbah*




## በበድር ኢትዮጵያ የሴቶች ዳእዋ ግሩፕ ተዘጋጅቶ የቀረበ

**"ጌታችሁንም ምህረት ጠይቁ። ወደ እርሱም (በንስሃ) ተመለሱ።..." (11:3)**

***" እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እውነተኛ ንስሃ በመግባት ወደ አላህ ተመለሱ። ጌታችሁ ሃጢአቶቻችሁን ይሰርይላችኋል።..." (66:8)***

**ተውባህ** የሚለው ቃል በአረብኛ ቋንቋ "መመለስ" ማለት ሲሆን በኢስላማዊ ትርጉሙ ደግሞ እንድ ሰው አላህ ከከለከላቸው ነገሮች ተቆጥቦ እርሱ ወዳዘዘው ተግባራት መመለስ ማለት ነው። ተውባህ በአላህ ለሚያምኑ ሰዎች በሙሉ አስፈላጊና አንገብጋቢ ርእስ ሲሆን ለእያንዳንዱ ሙስሊም እንዲያውም ለእያንዳንዱ አማኝ የቀጣይ አለም ሂዎት ውጤታማነት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይህም አባባል በሚቀጥለው የቁርአን አንቀጽ ይደገፋል፤

**"አማኞች ሆይ ትጸዱ ዘንድ ሁላችችሁም ወደ አላህ በመመልስ ተጸጸቱ" (ኑር 31)**

የተውባን ታላቅ ስፍራ እና ጥቅም በሰፊው የተነገረ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የአላህን ውዴታ እና ደስታን ማስገኘቱ አንዱ ነው። አላህ (ሱወ) ይህንን አስመልክቶ በተለያዩ የቁርአን አንቀፆች የገለፅ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በሱረቱል በቀራህ ውስጥ አላህ እንዲህ ይለናል፣

"...አሏህ (ከሃጠአት) ንስሃ የሚገቡትን ፤(ከፀያፍ አድረጎቶች) ራሳቸውን የሚያፀዱትንም በእጅጉ ያፈቅራል በላቸው።" [2:222]

አንድ ሰው ተውባህ ሲያደርግ አላህ በጣም ይደሰታል። አነስ ኢብን ማሊክ (ረዓ) የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ መናገራቸውን አስተላልፈዋል፦ “ከናንተ አንዳችሁ ምድረ በዳ መሬት ላይ ያጣትን ግመሉን በድንገት ሲያገኝ ከሚሰማው ደስታ የበለጠ አላህ በባሪያው ተውባህ ይደሰታል።” ብለዋል (ቡኻሪና ሙስሊም)

የተፈጸመው ወንጀል በሰውየውና በአላህ መካከል ብቻ ተውስኖ የሚቀር እና ከሰው መብት ጋር ያልተነካካ ከሆነ ከእንዲህ አይነቱ ወንጀል ለመቶበት ሶስት ቅድመ መስፈርቶች (ሸርጦች) መሟላት አለባቸው፤

1. ሰውየው ወንጀሉን ማቆም አለበት

2. ለሰራው ሃጢአት እና ለፈጸመው ጥፋት መቆጨት ይኖርበታል።

3. ወደፊት እንዲህ አይነቱን ሃጢአት ዳግም ላለመፈጸም ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ከነኝህ ሶስት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ከጎደለ ተውበቱ ተቀባይነት የለውም። ወንጀሉ ከሰዎች ሃቅ ጋር የተያያዘ ከሆነ ለተውበት አራት ቅድመ ሁኔታዎች መሞላት አለባቸው። እነዚህም ከላይ የተጠቀሱት ሶስት ነጥቦች እና አራተኛ ከሰውየው ሃቅ መጽዳት ነው። ገንዘብ እና መሰል ነገሮችን መመለስ ሲኖርበት በሃሜት ስሙን አጥፍቶ ከሆነ ደግሞ ተገቢውን ይቅርታ ይጥይቃል።

የአላህ መልእክተኛ ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አቡ ሁረይራ (ረዓ) አስተላልፈዋል፤

“እኔ በየቀኑ ከሰባ ጊዜ በላይ አላህን ምህረቱን እማጸናለሁኝ፣ ወደርሱም እመለሳለሁኝ። (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

አላህ(ሱወ) በለሊት እጁን ይዘረጋል፦ ቀን ጥፋት የፈጸመ ተውበት ያደርግ ዘንድ፤ በቀን እጁን ይዘረጋል በለሊት ጥፋት የፈጸመ ተውበት ያደርግ ዘንድ፦ ጸሃይ በመግቢያዋ እስከምትወጣበት ዕለት ድረስ።” (ሙስሊም ዘግበውታል)

የአላህ መል እክተክኛ ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አቡ ሁረይራ (ረዓ) አስተላልፈዋል፤

“እኔ በየቀኑ ከሰባ ጊዜ በላይ አላህን ምህረቱን እማጸናለሁኝ፣ ወደርሱም እመለሳለሁኝ። (ቡኻሪ እና ሙስሊም)

አላህ(ሱወ) በለሊት እጁን ይዘረጋል፦ ቀን ጥፋት የፈጸመ ተውበት ያደርግ ዘንድ፤ በቀን እጁን ይዘረጋል በለሊት ጥፋት የፈጸመ ተውበት ያደርግ ዘንድ፦ ጸሃይ በመግቢያዋ እስከምትወጣበት ዕለት ድረስ።” (ሙስሊም ዘግበውታል)

## የምንጣራቸው ቁም ነገሮች

የአላህ (ሱወ) ለባሪያዎቹ ያለው እዝነትና ይቅር ባይነት የጊዜ ገደብ የሌለው እንዲሁም የምህረት በሩ ዘወትር ክፍት መሆኑን ከላይ በተጠቀሱት አንቀጾች እና ሃዲሶች እንመለከታለን። የአላህ ምህረት ለማንኛውም ምህረቱን ፈላጊ ሰው በሙሉ የተሰጠ ነው። ይህም ነቢይ፣ ሲዲቅ፣ አማኝ፣ እንዲሁም በወንጀል የተዘፈቀ ሙስሊም ሁሉ ያጠቃልላል። መልእክተኛው ከወንጀል የተጠበቁና አላህ ጥቃቅን ነገሮች ሁሉ የማራቸው ከመሆናቸው ጋር በቀን 70 ጊዜ ምህረትን ይጠይቁ ነበር። ይህም በሙስሊሙ ላይ የተውበት ስሜት እንዲዳብር ግፊት ለማሳደር የተደረገ ነው።
***እናንተ አማኞች ሆይ! ጊዜው ሳያልፍ ወደ አላህ ተመለሱ። በሰራችሁት ወንጀል ተፅፅታችሁ ይቅርታውን ለምኑት፣ አላህ (ሱወ)ከጠየቁት ወንጀልን በሙሉ መሃሪ ጌታ ነውና።*** ምህረት መጠየቅ በማንኛውም ሰው ላይ ግዴታ ነው።